# በዋሺንግተንዲሲ የዲሴምበር 17 2017 የተደረገ የሕዝባዊ ሥብሰባ ዘገባ

ባለፈው ዕሁድ ዲሴምበር 17 2017 በዚህ በዋሺንግተን ዲሲ መዲና በድምቀት ተከናወነ። በሰማያዊ ፓርቲ፤መኢአድና የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራትግል ሸንጎ የተጠራው ሕዛባዊ ሥብሰባ በተሰካ ሁኔታ መጠናቀቁን ቀላቀባያችን በቦታው ተገኝቶ ዘግቦልናል። ይህን ታሪካዊ ጉባዔ ልዩ የሚያደርገውም ከላይ የተዘረዘሩት ሦስት ድርጅቶች ለረጅም ጊዜ ተካታታይ ውይይቶችን ካደረጉ በሁዋላ በጋራ ለመስራት መስማማታቸውን ይፋ ማድረጋቸው ሲሆን የድርጅቶቹ መሪዎች ፊርማቸውን ያሰፈሩበት ልዩ መግለጫ በእለቱ ለሕዝብ ተሰራጭቷል።



በጉባዔው ላይ በዶ/ ር አክሎግ ቢራራ መክፈቻ ንግግር  እና ደ/ር ፍቅሬ ቶለሳ (በስካይፐ) በማከታተል ባቀረቡት ንግግር የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ የተንተራሰ ሰፊ ገለጻ ያደረጉ ሲሆን ዶ/ ር አክሎግ ከበፊታችን ተደቅኖ ያለውን አደገኛ የጎሳ ተከለ ችግር ለመታደግ ዋነኛ መፍትሄው በኢትዮጵያ ላይ ያተኮረ ብሔራዊ መግባትን የመፍጠርን አስፈላጊነት አሳስበዋል። ዶ/ር ፍቅሬ ቶለሳ በማስከተል ባቀረቡት ንግግር ብዙ ክፍለ አገሮች ባላት ኢትዮጵያ የሕዝቦችዋ ባህል፣ ቁንቋና እምነት የሚከበርበት ሥርዓተ መዋቅርን  መዘርጋት አስፈላጊነት አስምረውበታል። የሰማያዊ ፓርቲ ልቀመንበር አቶ የሸዋስ አሰፋ፤ የመኢአድ ፕሬዝዳንት ዶ/ ር በዛብህ ደምሴና የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራትግል ሸንጎ ልቀመንበር ዶ/ ርታዬ ዘገየ በማከታተል ለውይይት ጠቃሚ የሆነ መነደርደሪያ አቅርበዋል።

የመኢአድ ፕሬዝዳንትደ/ር በዛብህ ደምሴ አማራጭ ” የፖለቲካ ድርጅት በኢትዮጵያ እንዴት በሚል ርዕስ በቀረቡት ንግግር በኢትዮጵያ የተካሄዱ ትግሎች ተመክሮ በምሳሌነት በማጣቀስ፣የሰላማዊ ትግልን አሸናፊነትና ትግሉንም ባንድነት

አቀናጅቶ የማካሄድን አስፍላጊነት አብክረው አስገንዝበዋል።



የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ የሽዋስ አሰፋም “ ” ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ አስፈላጊ ነው በሚል ርዕስ ያቀረቡትን ሲያብራሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ አስፈላጊነት የማያጠያይቅ መሆኑን አስረግጠው፤ ነገር ግን እንዴት በሚለው አብይ ጉዳይ አተኩረው በሃያ- አንደኛው ክፍለዘመን የቅራኔ መፍቻ ዘዴ ሥልጣንን በዱላ መቀባበል መሆን የለበትም ሲሉ በማስገንዘብ በአገርውስጥ የምንታገል ፓርቲዎች የሥርዓትን ለውጥ ለማምጣት የምንጠቀምበት መንገድ ጠብመንጃ መሆን የለበትም ሲሉ በማስረገጥ ለለውጥ የሚደረገው ትግል ከክላሽ ወደ ካርድ መቀየር አለበት ሲሉ አጽንዖት ሰጥተዋል።



በመጨረሻው ተናጋሪ የነበሩት የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግልሸንጎ ልቀመንበር ዶ/ር ታዬ ዘገየ የፓርቲዎች ሕብረትና ያኢትዮጵያ ሕዝብትግል በሚልርዕስ ዙሪያ ባደረጉት ንግግር፤አገሪቱ ውስጥበ ተጨባጭ የታየው ወቅታዊ ሁኔታ፤የገዢው እንደ ወትሮው እየረገጠ መግዛት ያልቻለበት በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝብ አሻፈረኝ አልገዛም ያለበት ሁኔታ ላይ የደረሰን መሆኑን ያመላከቱ ሲሆን በሦስቱ ፓርቲዎችመካከል የተካሔደውን የስምምነት ሰነድ ይፋ በማድረግ ሦስቱም ተናጋሪዎቹ የውይይት መንደርደሪያ ንግግራቸውን አጠናቋል።
የእለቱን የስብሰባ መርሀ ግብር በመምራት የተባበረው ታጋይ አክቲቪሰት ናጋዜጠኛ አቶ አበበ በለው ነበር። የፓርቲዎቹ

ወኪሎች ከስብሰባ ታዳሚዎች ጋር ጠቃሚ ውይይትት አካሂደዋል።



በዝግጅቱ መሀልም በፕሮፌሰር አቻሜለህ ደበላ የተበረከተ ሥእል ለጨረታ ቀርቦ የተሰበሰበው ተዋጽኦ ወደ አገራቸው የስራ ጉብኝታቸውን አጠናቀው ለሚመለሱት የመአድና የሰማያዊ ፓርቲ በአገርቤት ለሚካሄዱት ትግል እንዲውል ተበርክቶ ስብሰባው በተሳካሁኔታተጠናቋል።
በሥፍራው ከተገኙ የዜናና የመረጃተ ቋሞችም ውስጥ የአሜሪካድምጽ(ቪ.ኦ.ኤ) ፤አባይ ሚድያ ፤አዲስ ድምጽ፣ ኢትዮፓናሮማእናራድዮ- ድሞክራሲያይገኙበታል።
ኢትዮፓኖራማ
ዲስምበር 2017